# በጣሊያን የኢፌዲሪ ኤምባሲ ከኮሴንሳ ፕሮቪንስ ጋር በመተባበር ያዘጋጀው የኢንቨስትመንትና ንግድ ፕሮሞሽን ፎረም በኮሪሊያኖ ከተማ ተካሄደ

በጣሊያን የኢፌዲሪ ኤምባሲ ከኮሴንሳ ፕሮቪንስ አስተዳደር ጋር በመተባበር ያዘጋጀው የኢንቨስትመንትና ንግድ ፕሮሞሽን ፕሮግራም በኮሪሊያኖ ከተማ ከሃምሳ በላይ የሚሆኑ በተለያዩ መስኮች የተሰማሩ የካምፓኒዎች ባለቤቶች የፕሮቪንሱ ፕሬዚዳንት፣ የኮሪሊያኖ ከተማ ከንቲባና ሌሎች ባለሥልጣናት በተገኙ ብት እ.ኤ.አ ኤፕሪል 4/2014 ተካሂዷል፡፡

በዚሁ ፕሮግራም በሃገራችን ስላሉ የኢንቨስትመንትና የንግድ እድሎች በክቡር አምባሳደር ሙሉጌታ አለምሰገድ እና በቢዝነስ ጉዳዮች ዘርፍ ኃላፊ አቶ ሄኖክ ሃ/ገብርዔል ገለጻ የተደረገ ሲሆን፤ የፕሮቪንሱ ፕሬዚዳንት ሚ/ር ማሪዮ



ኦሊቬሪዮ፣ የፕሮቪንሱ ም/አፈ-ጉባዔና የኮሪሊያኖ ከተማ ከንቲባ በካላብሪያ ክልልና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ግንኙነት በኢንቨስትመንትና ንግድ መስክም ይበልጥ ሊጠናከር እንደሚገባው ክልሉም ለዚህ ዝግጁ መሆኑን የገለፁ ሲሆን፣ ፕሬዚዳንቱና ም/አፈ-ጉባዔው በጃንዋሪ 2014 ከፕሮቪንሱ በሃገራችን የቅድመ-ኢንቨስትመንት ጉብኝት ያደረገውን የቢዝነስ ልዑካን በመምራት ኢትዮጵያን

በጉበኙበት ወቅት የተመለከቱትን የሃገራችንን መልካም ገጽታ ለተሳታፊዎች አብራርተዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከጥቂት ወራት በፊት በሃገራችን ኢንቨስት ያደረገ Technology Drilling Srl የተባለ የክልሉ ካምፓኒ ባለቤት በሃገራችን ኢንቨስት በማድረግ ረገድ የነበራቸውን ተሞክሮ ለታዳሚዎች አካፍለዋል፡፡



በመቀጠልም በፕሮሞሽኑ የተሳተፉና በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጐት የሚያሳዩ ካምፓኒዎች የሚገኙበት የቢዝነስ ልዑካን ቡድን በመጪው ሜይ/2014 ወር መጨረሻ በሃገራችን የቅድመ-ኢንቨስትመንት ጉብኝት እንዲያደርግ ከመግባባት ላይ በመድረስ የፕሮሞሽን ፕሮግራሙ ተጠናቋል፡፡

ከዚህ ባሻገር ክቡር አምባሳደር ሙሉጌታ አለምሰገድ በፕሮሞሽኑ የተሳተፉና በሃገራችን ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጐት ያሳዩ የባቡርና የመኪና ክፍሎችን በመገጣጠም፣ ፓስታ በማምረት፣ በትራክተር ማከፋፈልና በቆሻሻ recycling ላይ የተሰማሩ አራት ካምፓኒዎችን ጉብኝተዋል፡፡



በተጨማሪም በኮንሴንሳ ዩኒቨርሲቲ በመገኘት በሃገራችንና በዩኒቨርሲቲው መካከል ያለው ግንኙነት ሊጠናከር በሚችልበት ሁኔታ ላይ ከዩኒቨርሲቲው ምክትል ዲን እና ሌሎች የዩኒቨርሲቲው ኃላፊዎች ጋር ተወያይተዋል፡፡ በተጨማሪም በዩኒቨርሲቲው የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ ሶስት ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎችን በማግኘት አነጋግረዋል፡፡ ከዩኒቨርሲቲው ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ውይይት ዩኒቨርሲቲው ስለሚሰጣቸው የትምህርት ዓይነቶች ኃላፊዎቹ ገለጻ ያደረጉ ሲሆን፤ ከሃገራችን ጋር ያለው ግንኘ ኁነት እንዲጠናከር እንደሚፈልጉና ከሃገራችን ለሚላኩ ተማሪዎች ተጨማሪ የስኮላርሽፕ እድሎችን መስጠት ስለሚቻልበት ሁኔታ ለወደፊቱ በጋራ መስራት እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡

በሃገራችንም በኩል ግንኙነቱ እንዲጠናከር ከፍተኛ ፍላጐት መኖሩን በመግለጽ ዩኒቨርሲቲው ለሃገራችን ተማሪዎች ተጨማሪ የስኮላርሽፕ እድሎችን ለመስጠት ፍላጐት በማሳየቱ ክቡር አምባሳደር ሙሉጌታ አመስግነዋል፡፡